# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

# *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)

ሚያዝያ ፲ ቀን ፪ ሺህ ፮ ዓ. ም
April 18, 2014

## በደቡብ አፍሪቃ ውስጥ በኢትዮጵያውያን ላይ የሚደርሰውን ዘግናኝ ጭፍጨፋ ኢህአፓ(ዴሞክራሲያዊ) ያወግዛል!

በደቡብ አፍሪቃ ውስጥ የአናሳ ነጮችን የዘረኛ አገዛዝ በመቃወም ለመብታቸው የታገሉ ጥቁር አፍሪቃውያን በታሪክ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለዋል። እነማንዴላና ሌሎች ቆራጥ የዴሞክራሲ ሥርዓት ታጋዮች፣ የአናሳ ነጮች የዘረኛ አገዛዝ እንዲቀር ጥረው ግረው፣ የትግል ውጣ ውረዱን አልፈው ጫፍ ሲያደርሱ ዓላማቸው ጥቁር አፍሪቃውያን በአገራቱ ውስጥ በነፃነትና በመከባበር አብረው እንዲኖሩባት ነበር። በትግላቸው ወቅት በነቂስ መላው አፍሪቃ፣ ከመንግሥት እስከ ተራ ዜጋ ድረስ፣ የትግላቸው ደጀን በመሆን፣ አይዞን እያለ እስከ ነፃነታቸው ቀን ድረስ አብሯቸው ተጉዟል። ሰሞኑን ግን በዚያች አገር ውስጥ እየተደረገ ያለው ተግባር ከሰው ልጅ ርኅራሄ ውጭ የሆነ አሰቃቂ ግድያና ድብደባ ከትግሉ ዓላማ ውጭ የሆነ፣ ከዚያም አልፎ እጅግ ዘግናኝና አስከፊ የሆነ ድርጊት ነው። በነጭ ጭቆና ሥር ኖሮ፣ ግፍና ሰቆቃ ምን መሆኑን የተመለከተ፤ ለዴሞክራሲና ለሰው ልጅ መብት ከታገለ ሕዝብ እንዲህ ዓይነት ጭካኔ የሚታሰብ አልነበረም። ይህን ተግባር ከሁሉ የከፋ የሚያደርገው ደግሞ፣ የደቡብ አፍሪቃ ሕዝብ በትግሉ ወቅት የአፍሪቃ መንግሥታትና ሕዝቦቿ ከጎኑ በመሰለፍ እስከ የነፃነት ቀኑ ድረስ አብረውት እንደተጓዙ እንዲህ በአጭር ጊዜ መዘንጋቱ ነው። ኢትዮጵያ ለደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች ባለውለታ አገር ነች። ከዘረኛው የአናሳ ነጭ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት ሲታገሉ ከፍተኛ ዕርዳታ ያደረገች ኢትዮጵያ ናት። ወርቅ ላበደረ ጠጠር ይሏል ይህ ነው።

እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር በ1951 ዓ. ም የተባበሩት መንግሥታት ባወጣው ዓለም-አቀፍ የስደተኞች መብት መሠረት፣ አንድ ሰው ወይም ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች በአገራቸው መኖር አቅቷቸው ወደ ሌላ አገር ከተሰደዱ፣ በተሰደዱበት አገር ከፍተኛ ወንጀል እስካልፈጸሙ ድረስ በጥገኝነት የመኖር መብታቸው የተከበረ ነው። አሁን በደቡብ አፍሪቃ እየተሳደዱ፣ ድብደባ እየተፈጸመባቸው ያሉት አፍሪቃውያን የጠበቁት ደቡብ አፍሪቃውያን በስደት ጊዜያቸው የተሰጣቸውን በሰላም የመኖር መብት እንዲያገኙ ነበር። በአንፃሩ ግን ሰሞኑን በደቡብ አፍሪቃ እየተደረገ ያለው ጭካኔ የተሞላበት ግድያና

**P.O.Box 8141**
**Silver Spring, MD 20910**

**P.O.Box 88675**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 202- 241 2078**

**Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

ድብደባ ግን የዓለም-አቀፍን ሕግ ከመጣሱም በላይ በግልጽ ሰው የመሆን ሥነ-ባህሪ የጎደለው ድርጊት ነው። ምናልባትም ይህንን የፈጸመው መንግሥት ሳይሆን ሕዝብ ነው ሊባል ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን፣ መንግሥት ባለበት አገር ውስጥ የሰውን ልጅ እንደአውሬ እያሳደዱና የመኪና ጎማ ከአንገታቸው እያሰገቡ ቤንዚን አርከፍክፈው ሲያቃጥሏቸው እየታየ፣ ከመንግሥት የፀጥታ አስከባሪዎች በኩል ምንም ዓይነት የሕይወት ማዳን ሙከራ አለመደረጉ እጅግ አሳዛኝ ነው፣ መንግሥት አለ ለማለትም አያስደፍርም። ምናልባትም ገዳዮች እንደሚሉት በአገራችን ውስጥ ስደተኞች ልንሰራ የምንችለውን ሥራ ሁሉ እየቀሙን በመሆናቸው ይውጡልን በሚል ከሆነም፣ ሕጋዊ በሆነ መንገድ የአገራቸው መንግሥት እንዲያስውጣላቸው መጠየቅ መብታቸው ሊሆን ሲገባ፣ አውሬነትን የተላበሰ፣ ኢ-ሰብአዊ እርምጃ በወገን አፍሪቃውያን ላይ መውሰዳቸው በምንም መልኩ ተቀባይነት አይኖረውም፤ ሊኖረውም አይገባም። እንዲያው በደፈናው፣ ጉዳዩ በሰው ልጅ አዕምሮ ሲታሰብ፣ ቅጥ ያጣ አውሬነት ነው። አውሬው ጅብ እንኳን ወገኑን አይበላም።

ስለዚህም፣ ይህን ዓይነት ከሰው ልጅ አስተሳሰብ ውጭ የሆነ ጭካኔ የተሞላበትን ግድያና ድብደባ ኢ.ሕ.አ.ፓ (ዴሞክራሲያዊ) እጅግ በጣም አድርጎ ያወግዛል። የደቡብ አፍሪቃ መንግሥትም ይህን የመሰለ ተግባር እንዳይደገም የማድረግ ግዴታውን እንዲወጣ ኢ.ሕ.አ.ፓ(ዴሞክራሲያዊ) በጥብቅ ይጠይቃል። በሀገሪቱ ሰላም የማስፈን፣ የሰውን ሕይወት መጠበቅ የማንም መንግሥት ግዴታ ነውና።

በዚህ የጭካኔ አገዳደል ሕይወታቸው ያለፈ ወገኖቻችንን ነፍስ ይማር፤ ለቤተሰቦቻውም መጽናናቱን ይታደጋቸው።

ዓለም-አቀፋዊው የስደተኞች መብት ይከበር!